«የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶቹ የተወሰዱት ከአሮጌው ትርጉም ነው።»

«የቁርአን ጥቅሶች የተወሰዱት በ38 ኛው ዘመን ከታተመው የቁርአን መጽሐፍ ነው።»

ውድ አንባቢ፥ በብሉይ ኪዳን በቶራ፥ ውስጥ አብርሃም የገዛ ልጁን ለመሥዋዕትነት አሳልፎ የሰጠበትን ዝርዝር ከመጽሐፍ ቅዱስ ብናነብ እንዲህ ይላል:-

ኦሪት ዘፍጥረት 21

33 አብርሃምም በቤርሳቤህ የተምር ዛፍን ተከለ፤ በዚያም የዘላለሙን አምላክ የእግዚአብሔርን ስም ጠራ።

34 አብርሃምም በፍልስጥኤም ምድር ብዙ ቀን እንግዳ ሆኖ ተቀመጠ።

ኦሪት ዘፍጥረት 22

1 ከእነዚህም ነገሮች በኋላ እግዚአብሔር አብርሃምን ፈተነው፥ እንዲህም አለው:- አብርሃም ሆይ። አብርሃምም እነሆ፥ አለሁ አለ።

2 የምትወደውን አንድ ልጅህን ይስሐቅን ይዘህ ወደ ሞሪያም ምድር ሂድ፤ እኔም በምነግርህ በአንድ ተራራ ላይ በዚያ መሥዋዕት አድርገህ ሠዋው አለ።

3 አብርሃምም በማለዳ ተነሥቶ አህያውን ጫነ፥ ሁለቱንም ሎሌዎቹንና ልጁን ይስሐቅን ከእርሱ ጋር ወሰደ፥ እንጨትንም ለመሥዋዕት ሰነጠቀ፤ ተነሥቶም እግዚአብሔር ወዳለው ቦታ ሄደ።

4 በሦስተኛውም ቀን አብርሃም ዓይኑን አነሣና ቦታውን ከሩቅ አየ።

5 አብርሃምም ሎሌዎቹን አላቸው:- አህያውን ይዛችሁ ከዚህ ቆዩ፤ እኔና ልጁ ወደዚያ ሄደን እንሰግዳለን፥ ወደ እናንተም እንመለሳለን።

6 አብርሃምም የመሥዋዕቱን እንጨት አንሥቶ ለልጁ ለይስሐቅ አሸከመው፤ እርሱም እሳቱንና ቢለዋውን በእጁ ያዘ፥ ሁለቱም አብረው ሄዱ።

7 ይስሐቅም አባቱን አብርሃምን ተናገረው:- አባቴ ሆይ አለ። እርሱም:- እነሆኝ ልጄ አለው። እሳቱና እንጨቱ ይኸው አለ፤ የመሥዋዕቱ በግ ግን ወዴት ነው? አለ።



8 አብርሃምም:- ልጄ ሆይ፥ የመሥዋዕቱን በግ እግዚአብሔር ያዘጋጃል አለው ሁለቱም አብረው ሄዱ።

9 እግዚአብሔር ወዳለውም ቦታ ደረሱ፤ አብርሃምም በዚያ መሠዊያውን ሠራ፥ እንጨትንም ረበረበ፤ ልጁን ይስሐቅንም አስሮ በመሠዊያው በእንጨቱ ላይ አጋደመው።

10 አብርሃምም እጁን ዘረጋ፥ ልጁንም ያርድ ዘንድ ቢለዋ አነሣ።

11 የእግዚአብሔር መልአክም ከሰማይ ጠራና:- አብርሃም አብርሃም አለው፤ እርሱም:- እነሆኝ አለ።

12 እርሱም:- በብላቴናው ላይ እጅህን አትዘርጋ፥ አንዳችም አታድርግበት፤ አንድ ልጅህን ለእኔ አልከለከልህምና እግዚአብሔርን የምትፈራ እንደ ሆንህ አሁን አውቄአለሁ አለ።

13 አብርሃምም ዓይኑን አነሣ፥ በኋላውም እነሆ አንድ በግ በዱር ውስጥ ቀንዶቹ በዕፀ ሳቤቅ ተይዞ አየ፤ አብርሃምም ሄደ በጉንም ወሰደው፥ በልጁም ፋንታ መሥዋዕት አድርጎ ሠዋው።

14 አብርሃምም ያንን ቦታ ያህዌ ይርኤ ብሎ ጠራው፤ እስከ ዛሬም ድረስ በእግዚአብሔር ተራራ ይታያል ይባላል።

15 የእግዚአብሔር መልአክም አብርሃምን ከሰማይ ሁለተኛ ጊዜ ጠራው፥

16 እንዲህም አለው:- እግዚአብሔር:- በራሴ ማልሁ ይላል፤ ይህን ነገር አድርገሃልና፥ አንድ ልጅህንም አልከለከልህምና

17 በእውነት በረከትን እባርክሃለሁ፥ ዘርህንም እንደ ሰማይ ከዋክብትና በባሕር ዳር እንዳለ አሸዋ አበዛዋለሁ፤ ዘርህም የጠላቶችን ደጅ ይወርሳል፤

18 የምድር አሕዛብ ሁሉም በዘርህ ይባረካሉ ፥ ቃሌን ሰምተሃልና።

19 አብርሃምም ወደ ብላቴኖቹ ተመለሰ፥ ተነሥተውም ወደ ቤርሳቤህ አብረው ሄዱ፤ አብርሃምም በቤርሳቤህ ተቀመጠ።

ከቤርሳቤህ እስከ ኢየሩሳሌም ያለውን ርቀት እንደሆነ አስተውለን ልናጤነው ይገባል።

ኢየሱስ በስቅላት ከመሞቱ ከዘጠኝ ወራት በፊት አንድ በጥንቃቄ ሊጠብቁት የሚገባ ጉዳይ ላይ ትንቢት ተናገረ። ኢንጅል ውስጥ ሐዋርያው ጳውሎስ እንደዘገበው:-

> «ከዚያን ቀን ጀምሮ <u>ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ይሄድ ዘንድ</u> ከሽማግሌዎችና ከካህናት አለቆች ከጻፎችም ብዙ መከራ ይቀበልና <u>ይገደል ዘንድ በሦስተኛውም ቀን ይነሣ ዘንድ</u> እንዲገባው ለደቀ መዛሙርቱ ይገልጥላቸው ጀመር» (ማቴዎስ 16:21)።

ከላይ በተጻፈው ቃል መሠረት ኢየሱስ በኢየሩሳሌም በሚገኘው በሞሪያ ተራራ ላይ የሚሞት መሆኑን አስቀድሞ እንዳወቀው ግልጥ ነው። ሊሰቀል አቅራቢያም ይህን ሊጤን የሚገባውን ትንቢት በድጋሚ ተናግሮታል። ኢንጅል ይህን ቃል እንደሚከተለው ያቀርባል:-

> «አሥራ ሁለቱንም ወደ እርሱ አቅርቦ እንዲህ አላቸው:-<u>እነሆ ወደ ኢየሩሳሌም እንወጣለን፥ ስለ ሰው ልጅም በነቢያት የተጻፈው ሁሉ ይፈጸማል።</u> ለአሕዛብ አሳልፈው ይሰጡታልና፥ ይዘብቱበትማል ያንገላቱትማል ይተፉበትማል፤ <u>ከገረፉትም በኋላ ይገድሉታል፥ በሦስተኛውም ቀን ይነሣል</u>» (ሉቃስ 18:31-33)።

ስለሆነም ነቢያት እርሱን አስመልክተው የጻፉት ሁሉ ይፈጸም ዘንድ ኢየሱስ በኢየሩሳሌም ይሞት ዘንድ ግድ ሆነ። ገና ከጅምሩም ቢሆን፥ እግዚአብሔር የራሱ የሆነውን በግ በኢየሩሳሌሙ ሞሪያ ተራራ ለመሥዋዕትነት እንደሚያቀርብ ትንቢቱ በአብርሃም እንዲነገር አድርጓል።



### 3.ሦስተኛው ትንቢት የተነገረው በእግዚአብሔር መልአክ ነው:-

የእግዚአብሔር መልአክ ትንቢቱን ለአብርሃም እንዲህ ሲል ተናግሯል:-

> «<u>የምድር አሕዛብ ሁሉም በዘርህ ይባረካሉ</u>» (ኦሪት ዘፍጥረት 22:18)።

ለትውልድ ሁሉ የእግዚአብሔር በረከት ማስተላለፍያ ይሆናል ተብሎ የተነገረለት ከአብርሃም ዘር ማን ይሆን? ይህ ለመላ ዓለም ይደርሳል ተብሎ የሚነገርለት በረከትስ ምን ይሆን?

#### የሦስተኛው ትንቢት መፈጸም:-

እግዚአብሔር በአብርሃም ዘር በኩል ለመላ አሕዛብ ይደርስ ዘንድ ቃል የገባለት በረከት ምን ነበር? ለመልሱ ኢንጅል (ሓዲስ ኪዳን) በሐዋርያው ጳውሎስ የተጻፈውን ብናነብ:-

> «<u>መጽሐፍም እግዚአብሔር አሕዛብን በእምነት እንዲጸድቅ አስቀድሞ አይቶ</u>፥- <u>በአንተ አሕዛብ ሁሉ ይባረካሉ</u> ብሎ ወንጌልን ለአብርሃም አስቀድሞ ሰበከ» (ገላትያ 3:8)።

ስለዚህ በእምነት መጽደቅ (ደኅንነት) ከአሕዛብ መካከል፥ ለሚያምኑ ሁሉ ይደርስ ዘንድ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ታላቅ በረከት ነው።

ታድያ ለዚህ ታላቅ የእግዚአብሔር በረከት መተላለፊያ ይሆን ዘንድ የተመረጠ የአብርሃም ዘር ማን ይሆን? አሁንም ለመልሱ ሐዋርያው ጳውሎስን ከኢንጅል ብንጠቅስስ:-

> «<u>ለአብርሃምና ለዘሩም የተሰፋው ቃል ተነገረ</u>። ስለ ብዙዎች እንደሚነገር:- ለዘሮቹም አይልም፤ <u>ስለ አንድ እንደሚነገር ግን:- ለዘርህም ይላል፥ እርሱም ክርስቶስ</u>» (ገላትያ 3:16)።

የእግዚአብሔር በግ በሆነው፥ ከአብርሃም ዘር ይወጣል ተብሎ ተስፋ በተገባለት፥ በመሢሑ ኢየሱስ ለሚያምኑ አሕዛብ ሁሉ እግዚአብሔር ሊሰጥ ቃል የገባው ታላቅ በረከት በእምነት የሚገኝ ደኅንነት ነው።

የዓለምን ሕዝብ ያድን ዘንድ ኢየሱስ የእግዚአብሔር መሢሕ በመሆን ወደ ዓለም እንደሚዘልቅ አብርሃም ያውቅ ነበር ብሎ ማሰቡ የሚቻል ነውን? ኢየሱስ

ከመሞቱና ከመነሣቱ ከጥቂት ቀናት በፊት ለአይሁድ የተናገረውን ከኢንጅል ብንወስድ መልሱን እናገኛለን፡-

> «አባታችሁ አብርሃም ቀኔን ያይ ዘንድ ሐሤት አደረገ፥ አየም ደስም አለው። አይሁድም፡- ገና አምሳ ዓመት ያልሆነህ አብርሃምን አይተሃልን? አሉት። ኢየሱስም፡- እውነት እውነት እላችኋለሁ፣ አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ አላቸው» (ዮሐንስ 8፡56-58)።

ኢየሱስ ከአብርሃም በፊት ሕያው ሆኖ መኖሩን ግልጥ አድርጎታል። በተጨማሪም አንድ ቀን ኢየሱስ ሞትን አሸንፎ እንደሚነሣና በእርሱ ለሚያምኑ ሁሉ የዘላለምን ሕይወት እንደሚሰጥ በመገንዘብ አብርሃም መደሰቱን፣ ይህንንም ሁሉ ኢየሱስ እንደሚያውቅ እንመለከታለን። እነዚህ ነጥቦች በዚህም በዚያም የሚያጎሉት ኢየሱስ ከዕለተ ልደቱ ከብዙ ዘመናት በፊት ሕያው መሆኑን ነው።

ውድ አንባቢ፣ በቁርአን ዘገባ መሠረት በሱረቱ 37 አብርሃም የገዛ ልጁን ለመሥዋዕት ያቀረበበትን ክፍል እናገኛለን።

## ምዕራፍ 37፡ አል-ሷፍፋት

100 ጌታዬ ሆይ! ከመልካሞቹ የኾነን፣ (ልጅ) ስጠኝ።

101 ታጋሽ በኾነ ወጣት ልጅም አበሰርነው።

102 ከርሱ ጋርም ለሥራ በደረሰ ጊዜ፣ ልጄ ሆይ! እኔ በሕልሜ እኔ የማርድህ መኾኔን አያለሁ፤ ተመልከትም፤ ምን ታያለህ? አለው፤ አባቴ ሆይ! የታዘዝከውን ሥራ፤ አላህ ቢሻ ከታጋሾቹ ኾኜ ታገኘኛለህ አለ።

103 ሁለቱም ትእዛዙን በተቀበሉና በግንባሩም ጎን ላይ በጣለው ጊዜ፣ (የኾነው ኾነ)።

104 ጠራነውም፤ (አልነው)፡- ኢብራሂም ሆይ!

105 ሕልሙን በውነት አረጋገጥክ፤ እኛ እንደዚሁ መልካም ሠሪዎችን እንመነዳለን።

106 ይህ እርሱ በውነት ግልጽ ፈተና ነው።

107 በታላቅ ዕርድም (መሥዋዕት) ተቤዠነው።

108 በርሱም ላይ በኋለኞቹ ሕዝቦች ውስጥ መልካም ዝናን አስቀረንለት።



109 ሰላም በኢብራሂም ላይ ይኹን።

110 እንደዚሁ መልካም ሠሪዎችን ሁሉ እንመነዳለን።

111 እርሱ በእርግጥ ካመኑት ባሮቻችን ነው።

ይሁንና በመጽሐፈ ሕግጋት(ቶራኽ) የተዘረዘሩት ሦስቱም ትንቢቶች በቁርአን ውስጥ አይገኙም። ለመላ ዓለም ይደርስ ዘንድ፥ ከእግዚአብሔር የተሰጠን በረከት አስመልክቶ በኢንጅል ስለተዘገቡ ትንቢቶችና በመሢሑ በኢየሱስ ስለ መፈጸማቸው ቁርአን በአንዳቸውም ጊዜ አይጠቅስም።

ይሁንና ግን ቁርአን ኢየሱስ መሢሕ ስለ መሆኑ በምስክርነት ጽፏል፡-

> «መላእክት ያሉትን (አስታውስ)፡- መርየም ሆይ! አላህ፡ ከርሱ በሆነው ቃል ስሙ አልመሲሕ ዒሳ የመርየም ልጅ በዚህ ዓለምና በመጨረሻውም ዓለም የተከበረ ከባለሟሎችም በኾነ(ልጅ)፡ ያበስርሻል፤» (ምዕ.3 አሊ-ዒምራን 45)።

ስለዚህ ቁርአን ኢየሱስን መሢሕ መሆኑን ገሀድ አድርጎ፥ በይፋ ይናገርለታል፤ ለአሥራ አንድ ጊዜ መሢሑ ኢየሱስ እያለ ነጠቃቅሶት እንመለከታለን። ይሁንና ቁርአን ይህን ታላቅ የክብር ስም ያዘለውን ትርጉም በአንዳቸውም ጊዜ ግልጥ አላደረገም። ስለዚህም ቁርአን ላይ ብቻ ያተኮረ አንባቢ፥ መሲሕ የሚለው ድንቅና የጥልቅ ቁም ነገሮች ጥልቅ ቃል በውስጡ የቋጠረውን በረከት በሚገባ ሊያጤነው አይችልም፤ ስለዚህ ከቁርአን በፊት የነበሩ ቅዱሳን መጻሕፍት (ብሉይና አዲስ ኪዳን) በመደጋገምና በግልጥ አስፍረውታልና እነዚህን ጠንቅቆ ማንበብ ያሻል፥ ይህ ድንቅ ስም ያለውንም ትልቅ ስፍራ የሚሰጠውን በረከት በጥልቀት ለማወቅ ይቻለናል።

በተጨማሪም ቁርአን በመጽሐፍ ቅዱስ የተካተቱትን መጻሕፍት ከእግዚአብሔር የተገኙ ናቸው ብሎ በማረጋገጥ የክብር ቦታ ይሰጣቸዋል። በዚህ ላይ የተጻፉት ከቁርአን ሲነበቡ፡-

> «ሙሳንም መጽሐፍን በእርግጥ ሰጠነው፤» ምዕራፍ 2 አል-በቀራህ 87)።

> «በአላህና... በዚያም ነቢያት ሁሉ... በተሰጡት ... አመንን... በሉ» ምዕራፍ 2 አል-በቀራህ 136)።

> «...ለዳውድም ዘቡርን (መዝሙረ ዳዊት) ሰጠነው» (ምዕራፍ 4 አል-ኒሳእ 163)።

በፈለጎቻቸውም (በነቢያቶቹ ፈለግ) ላይ የመርየምን ልጅ ዒሳን፥ከተውራት በስተፊቱ ያለውን አረጋጋጭ ሲኾን አስከተልን፤ ኢንጅልንም (ወንጌልን) በውስጡ ቀጥታና ብርሃን ያለበት፥ በስተፊቱ ያለችውን ተውራትንም የሚያረጋግጥ፥ ለጥንቁቆችም መሪና ገሣጭ ሲኾን ሰጠነው» (ምዕራፍ 5 አል-ማኢዳህ 46)።

ቁርአን በመቀጠል እነዚሁ ከእግዚአብሔር የተገኙ መጻሕፍት ያሰፈሩዋቸው መልእክቶች እንዳይለዋወጡ ከራሱ ከእግዚአብሔር ጥበቃ እንደሚደረግላቸው ይናገራል። ቁርአንን በዚሁ ላይ ብንጠቅስ፡-

«...የአላህንም ንግግሮች ለዋጭ የለም፤» (ምዕራፍ 6 አል-አንዓም 34)።

«...የአላህ ቃላት መልለወጥ የላትም፤» (ምዕራፍ 10 ዩኑስ 64)።

በተጨማሪም ከጊዜያት በፊት የተገኙ የመጽሐፍ ቅዱስ የተለያዩ ጽሑፎችን ሊታመኑ እንደሚገባው አጥብቆ ይመክራል።

«እላንተ ያመናችሁ ሆይ! በአላህና ...ከበፊቱ ባወረደው መጽሐፍ፥ እመኑ፤» ምዕራፍ 4 አል-ኒሳእ 136)።

ውድ ወንድሜ፤ ከመሢሕ የሚገኝ በረከት በእርሱ ለሚያምኑ ሁሉ የሚደርስ በረከት ነው።

በሙሴ ሕግጋት፥ በነቢያት መጽሐፍትና በመዝሙረ ዳዊት የመሢሑን መምጣት አስመልክተው የተናገሩት ከኢየሱስና ስለ እርሱም ከተጻፈው ኢንጅል (አዲስ ኪዳን) ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት ነው። ከሙታን ከተነሣ በኋላ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ የተናገረውን ከኢንጅል ብንወስድ፡-

«ከእናንተ ጋር ሳለሁ በሙሴ ሕግና በነቢያት በመዝሙራትም ስለ እኔ የተጻፈው ሁሉ ይፈጸም ዘንድ ይገባል ብዬ የነገርኋችሁ ቃሌ ይህ ነው አላቸው። በዚያን ጊዜም መጻሕፍትን ያስተውሉ ዘንድ አእምሮአቸውን ከፈተላቸው፤ እንዲህም አላቸው፡- ክርስቶስ መከራ ይቀበላል በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ይነሣል፥ በስሙም ንስሐና የኃጢአት ስርየት ከኢየሩሳሌም ጀምሮ በአሕዛብ ሁሉ ይሰበካል ተብሎ እንዲሁ ተጽፎአል» (ሉቃስ 24፡44-47)።



መሢሑ ለመላ ዓለም ኃጢአት ሲል ተሠቃየ። በአሁኑ ጊዜ ኢንጅል (አዲስ ኪዳን) እንዲህ ይለናል፡-

«ኃጢአተኞችን ሊያድን ክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዓለም መጣ የሚለው ቃል የታመነና ሁሉ እንዲቀበሉት የተገባ ነው» (1ኛ ጢሞቴዎስ 1፡15)።

«ሰዎች ሁሉ ሊድኑና እውነቱን ወደ ማወቅ ሊደርሱ በሚወድ በእግዚአብሔር በመድኃኒታችን ፊት መልካምና ደስ የሚያሰኝ ይህ ነው። አንድ እግዚአብሔር አለና፥ በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ፥ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤ ራሱንም ለሁሉ ቤዛ ሰጠ» (1ኛ ጢሞቴዎስ 2፡4-6)።

«ክርስቶስ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር እንዲያቀርበን እርሱ ጻድቅ ሆኖ ስለ ዓመፀኞች አንድ ጊዜ በኃጢአት ምክንያት ሞቶአልና፤ በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ» (1ኛ ጴጥሮስ 3፡18)።

«እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው» (2ኛ ቆሮንቶስ 5፡21)።

«በዚህ ምክንያት ደግሞ እግዚአብሔር ያለ ልክ ከፍ ከፍ አደረገው፥ ከስምም ሁሉ በላይ ያለውን ስም ሰጠው፤ ይህም በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ፥ መላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደ ሆነ ይመሰክር ዘንድ ነው» (ፊልጵስዩስ 2፡9-11)።

ውድ አንባቢ ፤ መሢሑን እንደ አዳኝህ ትቀበለው ዘንድ ፈቃድህ ሆኖአልን? መሢሑ ኢየሱስን እንደ ጌታህና እንደ አዳኝህ ትቀበለውና ታከብረው ዘንድ እግዚአብሔር ፈቃዱ ነው። (ይህ ካነበብናቸው ሁሉ የሚስተዋል ነው)። የእግዚአብሔር በግ የሆነውን ኢየሱስን በተቀበልክ ጊዜ ለኃጢአትህ ሁሉ ይቅርታን ታገኛለህ። እግዚአብሔርም ሰማያዊ አባትህ እንደሆነ ታውቃለህ። መንግሥተ ሰማይም ትገባ ዘንድ ዋስትና ይኖርሃል። መሢሑ ኢየሱስን እንደ አዳኝህ ለመቀበል ዝግጁ ከሆንክ የሚከተለውን ጸሎት መጸለይ ትችላለህ።

ኃያሉ አምላክ ሆይ፥ በግህ የሆነው መሢሑ ኢየሱስን ወደ ዓለም በመላክህ አመሰግንሃለሁ። ለእኔ ያለህን ፍቅርም በመሢሑ ኢየሱስ በኩል ስለገለጥክልኝ አመሰግንሃለሁ። መሢሑ ኢየሱስ ያንተ የመሥዋዕት በግ ይሆን ዘንድ ፈቃድህ ስለሆነ አመሰግንሃለሁ። ለኃጢአቴ ይቅርታን አገኝ ዘንድ ሕይወቱ በመስቀል ላይ እንድታልፍ ስለፀቀድህ አመሰግንሐለሁ። የዘለዓለም ሕይወት ይኖረኝ ዘንድ ኢየሱስ ሞትን አሸንፎ በመነሣቱ አመሰግንሃለሁ። ኃጢአተኛ መሆኔን አውቃለሁ። ለኃጢአቴም ሁሉ ይቅርታን እለምንሐለሁ። የመሥዋዕት በግህ በሆነው በመሢሑ ኢየሱስ ሞት ምክንያት ያገኙሁትን የኃጢአት ይቅርታ በዚችው ደቂቃ ተቀብያለሁ። መሢሑ ኢየሱስ ጌታዬ እንዲሆን እሻለሁ። ኢየሱስ የሚወዳቸውን ያህል እኔም ሌሎችን ሁሉ እወድ ዘንድ ዕርዳታህ አይለየኝ። ኃጢአቴንም ከላዬ ላይ ስላነሣህልኝ አመሰግንሃለሁ። የራስህም አድርገህ ስለተቀበልከኝ አመሰግንሃለሁ። ይህንንም ሁሉ ጌታዬና አዳኜ በሆነው በመሢሑ ኢየሱስ ስም እለምንሃለሁ፤ አሜን።